# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# ደጉ ሳምራዊ፡፡



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot, Lazarus
Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Ruth Klassen, Sarah S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



“መምህር ! የዘላለምን ሕይወት አገኝ
ዘንድ ምን ላድርግ?” ይሄንን ጥያቄ
የጠየቀው ሰው ሕግ አዋቂ ነበረ ፣
ኢየሱስን ሊፈትነው ፈልጎ ነው፡፡



ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰለት
“የእግዚአብሔር ሕግ ምን ይላል?”


ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰለት ፣
“እግዚአብሔርንና ባልንጀራህን
እንደራስህ ውደድ”። አስከትሎም ፣
“ባልንጀራዬስ ማነው?”
ብሎ ጠየቀው።
3


የሰውየውን ጥያቄ ሊመልስለት፣ ኢየሱስ ስለ አንድ ከኢየሩሳሌም
ተነስቶ ወደ ኢያሪኮ ይሄድ ስለነበረ ሰው ነገረው።
ሰውየው በወንበዴዎች ጥቃት
የተፈጸመበት ነው።
4


ወንበዴዎቹ ያገኙበትን ነገር ሁሉ ወስደውበታል ፤ እድለ
ቢስ የሆነውን ተጓዥ ልብስ ሁሉ ሳይቀር ነው። እጅግ
አቁስለውትም ነበረ። በመንገዱ ዳር ላይ የሞት ጫፍ
አድርሰውት ትተውት ነበረ።
5


እንአጋጣሚ ፣ አንድ ካህን በመንገድ ያልፍ ነበረ።
በእርግጠኝነት ፣ የቆሰለውን ሰው ይረዳው
ይሆናል። በፍጹም ! የሰውየው ደም
እየፈሰሰ ሲመለከተው ፣
በመንገዱ በሌላኛው ጥግ አልፎ ሄደ።
6


በፍጥነትም ፣ የሚሰማው የእግር ኮቴ የሚናገረው ሌላ ሰው እየተቃረበ
እንደሆነ ነው። ሌዋዊ ነው፤ በመቅደስ ውስጥ ሆኖ ካህኑን
የሚያገለግል ሰው። እያለፈም የተጎዳውን ሰው ተመለከተ፤
ሳይረዳውም ጥሎት ሄደ።
7


በመጨረሻም ፣ ሳምራዊ ሰው ያልፍ ነበረ። አይሁዶች
ሳምራዊያንን ይጠሏቸው ነበረ። ኢየሱስ እየተናገረ
የነበረውን ታሪክ የሚሰሙ ሰዎች ሳምራዊው
የታሪኩ ዋና ሊሆን እንደሚችል አልጠበቁም
ነበረ። ነገር ግን ሆነ። ሳምራዊው ራራለት ፤ ሊረዳውም ቆመ።
8


ሳምራዊውም ተንበረከከ ፣ በተጎዳው ሰው ቁስል ላይ መድኃኒትና መጠቅለያን አድረገለት፡፡ ከዚያም የተጎዳውን ሰው በራሱ አህያ ላይ በመጫን ረዳው፡፡
9
በመንገድ ዳር ባለ የእንግዳ ማረፊያ ፣ ሳምራዊው ሰውየውን በእያንዳንዱ ምሽት ይንከባከበው ነበረ፡፡
10
በጠዋት ተነስቶ ተጓዡን ጉዳተኛ ደህና እስኪሆን ድረስ እንዲንከባከበው ለእንግዳ ማረፊያው ጠባቂ ገንዘብን ከፈለው፡፡
11
ታሪኩ አለቀ፡፡ ኢየሱስ ጠየቀ ፣ “ለዚህ ጉዳተኛ ሰው ማነው ባልንጀራው?”
12
ሕግ አዋቂው መለሰለት ፣ “ባልንጀራው ምሕረትን ያደረገለት ሳምራዊው ነው”
13
ኢየሱስም “ሂድ እና ይሔንኑ አድርግ፡፡” አለው፡፡ ባልንጀራ ማለት የቱኛውም አስፈልጎት ውስጥ ያለ ሰው ማለት ነው፡፡ በተለያየ አስፈልጎት ውስጥ ያሉትን በመርዳት ፍቅራችንን ልንገልጽ እንችላለን፡፡ ይሄ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል፡፡
14

ደጉ ሳምራዊ፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ሉቃስ 10

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

15

# መጨረሻ

46

60

16

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው፡፡

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል፡፡ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው፡፡ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል፡፡ ደግሞም ያደርገዋል፡፡ እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን፡፡

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ፡፡ እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ፡፡ ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ፡፡ አሜን፡፡

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16

17